ECCSA

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ
እና
የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት

የንግድ/የቢዝነስ አመራር እና የሰው ሀይል አስተዳደር

ኢትዮጵያ
ሚያዚያ 2014

ECCSA

የንግድ/የቢዝነስ አመራር እና የሰው ሀይል አስተዳደር

Business Management and Human Resource Management

የስልጠናዉ አላማ እና አስፈላጊነት

ECCSA

አዲስ ቢዝነስ ለመጀመር የሚያስፈልገን የገንዘብ አቅም

- የራስን ሀብት በመጠቀም
- ሼር በመሸጥ
- ከአጋር ጋር በመጣመር
- ከባንክ በመበደር ልናገኝ እንችላለን

ከባንክ ጋር አብረን ስንሰራ

- የተበደርነውን ብድር በተቀመጠልን የጊዜ ገደብ መክፈል ይኖርብናል። ለዚህ ደግሞ ድርጅታችን ዉጤታማ መሆን ይኖርበታል

የስልጠናዉ አላማ እና አስፈላጊነት

ECCSA

ድርጅታችን ውጤታማ ሆኖ ብድራችንን በተገቢው ሁኔታ ለመክፈል

- ድርጅታችንን በአግባቡ መምራት ይኖርብናል
- ደንበኞቻችንን በአግባቡ መያዝ ይኖርብናል
- ጥራት ያለዉ ምርት ማምረት ይኖርብናል
- ወጪአችንን እና ሌሎች ግብአቶችንን በአግባቡ መቆጣጠር ይኖርብናል
- ድርጅታችን በአስፈላጊው የሰው ሀይል (ሰራተኞችና መሪዎች) ማደራጀት ይኖርብናል

የስልጠናዉ አላማ እና አስፈላጊነት

ECCSA

ስለዚህ የዚህ ስልጠና ዋና አላማ ሰልጣኞችን

- ስለ ንግድ/ቢዝነስ አመራር
- ስለ ምርታማነት እና ውጤታማነት
- ስለ ምርት ጥራት
- ስለ የምርት ግብአት አያያዝ
- ስለ ክትትል እና ግምገማ
- ስለ የደንበኛ አያያዝ
- ስለ የሰው ሀይል አስተዳደር መሰረታዊ የሆነ ግንዛቤ እንዲያገኙ ለማድረግ ነው።

ECCSA

የንግድ ሥራ ምንድን ነው?

- ሰዎች በመሰባሰብ (ድርጅት በመመስረት) ወይም በተናጠል ፤ ምርቶችን (እቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን) ለደንበኞች በማቅረብ ትርፍ ለማግኘት የሚከናወን ተግባር ነው።

ECCSA

የንግድ ሥራ ድርጅት ምንድን ነው?

- ሰዎች በመሰባሰብ (ድርጅት በመመስረት) ወይም በተናጠል ፤ ምርቶችን (አቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን) ለደንበኞች በማቅረብ ትርፍ ለማግኝት የሚከናወን ተግባር ነው።

የንግድ/የቢዝነስ አመራር

ECCSA

የንግድ/ቢዝነስ አመራር (Business Management) ማለት፣ የማቀድን፣ የማደራጀትን፣ አስፈላጊውን የሰው ሃይል ማማላትን፣ የመምራትን እና የመቆጣጠርን ተግባራት የያዘ ሆኖ የአንድን የንግድ/ቢዝነስ አላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉትን ግብአቶች በማቀናጀት ውጤታማ እንዲሆን የሚያግዝን ሂደት ነው።

የቢዝነስ አመራር ዋና ዋና ተግባራት፣

- ማቀድ (Planning)
- ማደራጀት(Organizing)
- የሰው ሀይል ማማላት (Staffing)
- መምራት (Leadership)
- መቆጣጠር (Controlling)

የቢዝነስ አመራር አስፈላጊነት

- ምርታማነት
- ውጤታማነት
- ወጪ ቆጣቢነት


የንግድ/የቢዝነስ አመራር

ECCSA

የቢዝነስ ሰራ መሪ (Manager) ማለት፣ የንግድ/የቢዝነስን አላማ ከግብ ለማድረስ ኃላፊነትየተጣለበት ሰዉ ነዉ

የቢዝነስ ሰራ መሪ አይነቶች፣

- ዝቅተኛ ደረጃ (Lower level)
- መካከለኛ ደረጃ (Middle level)
- ከፍተኛ ደረጃ (Top Level)



የንግድ/የቢዝነስ አመራር

ECCSA

የዝቅተኛ መሪ ዋና ዋና ተግባራት

- የድርጅቱን የለት ተለት ተግባራትን ያቅዳል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል
- የድርጅቱን ሰራተኞች ያስተባብራል
- የድርጅቱን የአጭር ጊዜ እቅድ ያዘጋጃል

የንግድ/የቢዝነስ አመራር

ECCSA

የመካከለኛ ደረጃ መሪ ዋና ዋና ተግባራት

- የድርጅቱን ዋና ዋና ተግባራት ያቅዳል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል
- የድርጅቱን ዝቅተኛ መሪዎች ያስተባብራል
- የድርጅቱን የመካከለኛ ግዜ እቅድ ያዘጋጃል

የንግድ/የቢዝነስ አመራር

ECCSA

የከፍተኛ ደረጃ መሪ ዋና ዋና ተግባራት

- የድርጅቱን አጠቃላይ ተግባራት ያቅዳል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል
- የድርጅቱን መካከለኛመሪዎች ያስተባብራል
- የድርጅቱን የረጅም ግዜ እቅድ ያዘጋጃል
- ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ግንኙነት እና አጋርነት ይፈጥራል

የንግድ/የቢዝነስ አመራር

ECCSA

የንግድ ስራ መሪ ዋና ዋና ሚናዎች

- ከሌሎች ጋር መስራት
  - የወካይነት ሚና
  - የመሪነት ሚና
  - የቃላቀባይነት ሚና
- መረጃ ማእከል
  - መረጃ የመሰብሰብ ሚና
  - መረጃ የማሰራጨት ሚና
  - መረጃ የማስተላለፍ ሚና

የንግድ/የቢዝነስ አመራር

ECCSA

የንግድ ስራ መሪ ዋና ዋና ሚናዎች

- ውሳኔ መወሰን
  - የኢንተርፕሬነር ሚና
  - የመደራደር ሚና
  - ግብአት የማከፋፈል ሚና
  - ግጭትን የመፍታት ሚና

የንግድ/የቢዝነስ አመራር

ECCSA

የንግድ ስራ መሪ የሚያስፈልጉት ዋና ዋና ክህሎቶች

- የቴክኒክ (ከስራው ጋር ተዛማጅ የሆነ ክህሎት) (Technical skills)
- ሰውን የመምራት ክህሎት (Human skills)
- ሀሳባዊ (የጠቅላላ አዉቀት) ክህሎት (Conceptual skills)

የንግድ/የቢዝነስ አመራር

ECCSA

ዉጤታማ የሆነ የንግድ ስራ መሪ የሚያሳያቸው ባህሪያት

- ጠንካራ የመሪነት ክህሎት (Strong leadership skills)
- የተግባር ሰው መሆን (An action orientation)
- ርዕይ ያለው (A vision of where the firm is going)
- እጅግ በጣም ጥሩ የተግባቦት ክህሎት (Excellent communication skills)
- በራስ መተማመን (Self- confidence)
- ሪስክ የሚወስድ (The ability to take risks)
- የሚያነቃቃና የሚያበረታታ (The ability to motivate)
- እምነት የሚጣልበት (The ability to generate loyalty)
- የቡድን ስሜት የመፍጠር ክህሎት (Team building skills)
- ከስራዉ ጋር አግባብነት ያለዉ ክህሎት እና ልምድ (Technical skills & experience)
- አለማቀፋዊ እይታ ልምድ (International experience)

የንግድ/የቢዝነስ አመራር

ECCSA

የንግድ ስራ አመራር መርሆች

- የስራ ክፍፍል (Division of work).
- ስልጣንና ሀላፊነት (Authority & responsibility).
- ስርአት ማክበር(Discipline).
- ተጠሪነት (Unity of command).
- ለአንድ አላማ መቆም (Unity of direction).
- የሰራተኛ እና የድርጅት ፍላጎት ቅደም ተከተል (Subordination of individual interests to the general interest).

የንግድ/የቢዝነስ አመራር

ECCSA

የንግድ ስራ አመራር መርሆች

- ክፍያ(ደሞዝ እና ጥቅማጥቅም) (Remuneration).
- የተማከለና ያልተማከለ ውሳኔ (Centralization and Decentralization).
- የእዝ ሰንሰለት (Scalar chain).
- በትክክለኛው ቦታ (Order).
- አለማዳላት/ፍትሃዊነት (Equity).
- የተረጋጋ ሁሌታ መፍጠር (Stability and tenure of personnel).
- አዳዲስ ሃሳብ ማፍለቅ (Initiative).
- የቡድን ስሜት መፍጠር (Esprit de corps).

ምርታማነት

ECCSA

ምርታማነት እና ውጤታማነት ማለት የድርጅቱ የምርት ብዛት ከተጠቀምነዉ ግብአት ጋር በማነጻጸር ምን ያህል ዉጤታማ መሆናችንን የምናይበት ነዉ

ምርታማነት እና ውጤታማነት ለማምጣት:-

- የምርታማነት እና ውጤታማነት ግብ ማስቀመጥ
- መከታተል እና ግብረመልስ መስጠት
- ችግሮችን መፍታት
- እቅድ እና ቁጥጥርን ማመቻቸት
- ፈጠራን ማገዝ

ምርት ጥራት

ECCSA

የምርት ጥራት የተለያየ ትርጉም ያለዉ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ

- ከአላማ እና ከአገልግሎት ጋር መጣጣም
- የተሻለ ስራ በተሻለ ሰአት መስራት
- መጀመሪያዉኑ ከስህተት ነጻ ስራ መስራት
- የደምበኞችን ፍላጎት ማወቅና ማማላት
- ከስታንዳርድ ጋር መመሳሰል

የምርት ጥራት

ECCSA

የምርት ጥራት የደምበኞችን ፍላጎት ሲያማላ

- የደምበኞችን ርካታ ይጨምራል
- የምርቱን የመሸጥ እድል ያሰፋል
- ተወዳዳሪነትን ይጨምራል
- የገበያ ድርሻን ያሰፋል
- በተሻለ ዋጋ ይሸጣል
- ገቢን ያሳድጋል

የምርት ጥራት

ECCSA

የምርት ጥራት ከስህተት ነጻ የሆነ ምርት ሲመረት

- ስህተት ይቀንሳል
- ዳግም ስራን ይቀንሳል
- የደምበኞችን ርካታ እጦት ይቀንሳል
- የጥራት ፍተሻ እና ምርመራ ወጪን ይቀንሳል
- ምርታማነትን ይጨምራል
- ገቢን ያሳድጋል
- በጊዜ የማቅረብ አቅምን ይጨምራል

የምርት ጥራት

ECCSA

የምርት ጥራት ለማምጣት የሚወሰኑ ነገሮች

- የምርት ጥሬ ግብአት
- የአመራረት ሂደት
- የሰራተኞች ክህሎት እና ልምድ
- ምቹ አጋዝ ተቀማት (ዉሀ፤ መብራት)

የምርት ጥራት

ECCSA

የምርት ጥራት የሚገለጸበትነገሮች

- ዲዛይኑ በደንበኛ ፍላጎት ላይ መሰረት ያደረገ
- ከደንበኛ ፍላጎት ጋር መመሳሰል
- ደህንነት(በጤንነት ላይ ጉዳት የማያደርስ)
- በአግባቡ የተቀመጠ/ የተከማቸ

የምርት ግብአትን ማስተዳደር (አያያዝ)

ECCSA

የምርት ግብአት ማለት ድርጅታችን ምርት ለማምረት የምንጠቀማቸው ግብአቶች ይይዛል::

ግብአትን ስናስተዳድር

- መጀመሪያ ከትክክለኛ ቦታ ማግኘት፣ በትክክለኛ ዋጋ መግዛት፣ በትክክለኛ ግዜ ማቅረብ
- በትክክለኛ ቦታ ማከማቸት
- በቂ ቁጥጥር ማድረግ

ክትትል፣ ግምገማ እና ሪፖርት

ECCSA

ክትትል ማለት ድርጅታችንን የየእለት ተግባር የምንከታተልበት ሂደት ነው

ክትትሉ የሚካሄደው

- ስራን ከእቅድ ጋር በማነጻጸር
- የገንዘብ ወጪን ገበጀት ጋር በማነጻጸር
- የስራ ጥራትን ከስታንዳርድ ጋር በማነጻጸር

ግምገማ የድርጅታችንን ስራ ከውጤታማነት አንጸር የምንከታተልበት ሂደት ነው

ግምገማ የሚካሄደው፡-

- ከግበአት አንጻር
- ከአመራረት አንጻር
- ከምርት አንጻር
- ከውጤት አስፈላጊነት አንጻር
- ከዘላቂነት አንጻር

ክትትል፣ ግምገማ እና ሪፖርት

ECCSA

ሪፖርት ማለት፣ ድርጅታችንን የየለት ተግባር እና የውጤታማነትን ለሚመለከተው አካል የምናቀርብበት ሂደት ነው

ሪፖርት ስናደርግ

- ግልጽ መሆን አለበት
- የተሟላ መሆን አለበት
- ያልተንዛዛ መሆን አለበት
- እውነተኛ መሆን አለበት

የደምበኛ አያያዝ

- ደምበኛ ማለት የድርጅታችን ምርት ወይም አገልግሎት የሚጠቀሙ ናቸው
- ደምበኛ አያያዝ የረጅም ግዜ እና ትርፋማ ግንኙነት እንዲኖረን ያደርጋል

ECCSA

- የደምበኛ አያያዝ ጥቅም
  - ደምበኛን ለመያዝ
  - ደምበኛ ተኮር እንድንሆን
  - የደምበኛ አመኔታ ለማግኘት
  - ዋጋ ለመደራደር
  - የረጅም ግዜ (ተደጋጋሚ) ግንኙነት ለማግኘት

የሰው ሀይል አስተዳደር

ECCSA

- የሰው ሀይል አስተዳደር ማለት የድርጅታችንን አላማ ለማሳካት የሚያስፈልገንን የሰው ሀይል በጥራት እና በብዛት የምናማላበት ሂደት ነዉ።
- የሰው ሀይል አስተዳደደር ዋና ዋና ተግባራት
  - የሰው ሀይል እቅድ
  - ቅጥር፣ ምልመላ እና ምደባ
  - ሰልጠና
  - የስራ አፈጻጸም ምዘና
  - ዝዉዉር እና እድገት
  - የስራ ላይ ደህንነት
  - ደሞዝ እና ጥቅማጥቅም
  - ስንብት

የሰው ሀይል እቅድ

ECCSA

- የሰው ሀይል እቅድ ማለት ለድርጅታችን ወደፊት የሚያስፈልጉትን የሰው ሀይል በአይነት፣ ጥራት እና በብዛት በመገመት አስፈላጊውን እስትራቴጂ የምንነድፍበት ሂደት ነዉ።
- የዚህ ዕቅድ ዋና ዋና ተግባሮች ድርጅታችን አሁን ያለውን የሰው ኃይል ዓይነት ለይቶ በማወቅ በድርጅታችን ዕድገት ምክንያት ወደፊት የሚያስፈልገውን የሰው ሀይል ዓይነትና ብዛት መገመት እና በመጨረሻም የተዘጋጀውን የሰው ኃይል ዕቅድ ከፋይናንስ ዕቅድ ጋር ማቀናጀት ናቸው።
- የሰው ሀይል እቅድ ሂደት
  - ያለውን የሰው ኃይል ዓይነት፣ ብዛትና ደረጃ /Manpower Inventory/ ለይቶ ማወቅ፣
  - የድርጅታችንን ስትራቴጂክ ዕቅድ እና የፋይናንስ አቅም ከግምት በማስገባት ሊኖር የሚገባውን የሰው ኃይል ብዛት እና ደረጃ ካለው የሰው ኃይል ዓይነት፣ ብዛት እና ደረጃ ጋር በማነፃፀር ልዩነቱን ማወቅ፣
  - ወደፊት በጡረታ እና በተለያዩ ምክንያቶች የሚገለሉትን ሠራተኞች ብዛት እና ደረጃ እንዲሁም ጊዜውን በቅድሚያ መለየት፣
  - በዕድገት፣ በስንብት፣ በዝውውር፣ ወዘተ ምክንያት ክፍት ሊሆኑ የሚችሉትን የሥራ መደቦች በመገመት በሰው ኃይል አደረጃጀት ላይ የሚያመጡትን ለውጥ ማጤን፣

የሰው ሀይል አቅድ

ECCSA

- የሰው ኃይል ዕቅድ ከድርጅታችን ስትራቴጂክ ዕቅድ እንዲሁም ከፋይናንስ አቋም ጋር በማቀናጀት የሰው ኃይል ፍላጎት ማለት፣
  - ተጨማሪ የሰው ኃይል፣
  - ተተኪ የሰው ኃይል፣
  - ያለበቂ ሥራ የሚገኝ የሰው ኃይል፣ (redendent)
  - በሥልጠና አማካይነት ለተተኪነት ሊዘጋጁ የሚችሉ የሠራተኞች ብዛት፣ ዕውቀታቸውን በትምህርት የሚያሻሽሉ ሠራተኞች ብዛት፣ በዕቅድ ውስጥ ማጠቃለል፣

የሰው ሀይል ቅጥር እና ምልመላ

ECCSA

- የሰው ሃይል ቅጥር ማለት ድርጅታችን ተጨማሪ የሰው ሀይል በሚፈልግበት ወቅት አመልካቾች እንዲያመለክቱ የምንጋብዝበት ሂደት ነው
- የቅጥር
  - የዉስጥ
  - የዉጭ
- ቅጥር ለመፈጸም የምንጠቀማቸዉ መንገዶች
  - ማስታወቂያ
  - የትምህርት ተቀማት
  - ከስራ ፈላጊዎች ማመልከቻ

የሰው ሀይል ቅጥር እና ምልመላ

ECCSA

- ክፍት የስራ መደቦች ማስታወቂያ ይዘት
- ለክፍት የስራ መደቦች የሚወጣው ማስታወቂያ ቢያንስ የሚከተሉትን ይይዛል::
  - የስራ መደብ መጠሪያ
  - የደመወዝ ሁኔታ
  - ለስራ መደቡ የሚያስፈልገው የትምህርት አይነት፣ ደረጃ እና የስራ ልምድ
  - የስራ ቦታው
  - ማመልከቻ ለማቅረብ የተወሰነው የጊዜ ገደብ እና የመመዝገቢያ ቦታ
  - ዕጩው ማቅረብ ያለበት ሌሎች ማስረጃዎችና ሰነዶች
  - ድርጅቱ ለስራ መደቡ ለመቅጠር ያሰበው የሰራተኞች ብዛት
  - የቅጥሩ ሁኔታ በgሚነት ወይም በኮንትራት ስለመሆኑ
  - ለስራ መደቡ የሚያስፈልግ ልዩ ስልጠና(ካለ)።

የሰው ሀይል ቅጥር እና ምልመላ

ECCSA

- የሰው ሀይል ምልመላ ማለት አመልካቾችን በማወዳደር ለድርጅታችንና ለስራ መደቡ ብቁ የሆኑትን የምንመርጥበት ሂደት ነው
- የመምረጫ ዘዴዎች
  - ፈተና በመፈተን
  - ቃለ መጠይቅ በማድረግ
- ፈተና ወይም መጠይቅ ስናዘጋጅ
  - ከስራው ጋር ተዛማጅ መሆን አለበት
  - የሚያዳላ መሆን አለበት
  - በጥንቃቄ መያዝ አለበት

የሰው ሀይል ቅጥር እና ምልመላ

ECCSA

- የሰው ሀይል ምደባ ማለት አመልካቾችን በማወዳደር ለድርጅታችንና ለስራ መደቡ ብቁ የሆኑትን በመምረጥ ከተመረጠዉ/ ከተመረጠችዉ/ ከተመረጡት
- አመላካች/አመልካቾች ጋር ዉል በመያዝ፤ የስራ ምደባ የምናደርግበት ሂደት፤ ነዉ
- ለምደባ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች
  - ፈተና /ቃለ መጠይቅ ማለፍ
  - የህክና ማስረጃ
  - የፖሊስ ማስረጃ
  - በፊት ከሚሰራበት ማስረጃ
  - ምደባ እንደተከናወነ የሚሰሩ ተግባራት
  - የሰራተኛ ፋይል ማዘጋጀት
  - የማስተዋወቅ ስራ
  - የማሰልጠን ስራ
  - መታወቂያ መስጠት
  - የስራ መገልገያዎችና እቃዎች

የሰው ሀይል ቅጥር እና ምልመላ

ECCSA

- የስራ ውል አመሰራረት
- ድርጅታችን ሰራተኛውን በሚቀጥርበት ግዜ የቅጥር ደብዳቤ ይደርሰዋል::
- የሚመለከታቸው ክፍሎች በግልባጭ እንዲያውቁት ይደረጋል::
- የቅጥር ደብዳቤው የሚከተሉትን ይይዛል፣
  - የሰራተኛው ስም
  - የሰራተኛው የስራ መደብ፣ ከስራ ዝርዝር ተግባራት ጋር
  - የቅርብ ተቆጣጣሪ/ተጠሪነት
  - የስራ ቦታ
  - የስራ ክፍል
  - የስራ ደረጃ
  - የስራ ውሉ የሚጸናበት ጊዜ
  - የሚከፈለው ደመወዝ እና፣ የአከፋፈሉ ን ሁሌታና ጊዜ
  - አበል ካለ የአበሉን መጠን፣
  - የሙከራ ጊዜ

የሰው ሀይል ቅጥር እና ምልመላ

- የግል ማህደር

ECCSA

- ድርጅታችን ቢያንስ ቀጥለው የተዘረዘሩትን ማስረጃዎች አጠናቅሮ አዲስ በተቀጠረው ሰራተኛ የግል ማህደር ውስጥ ይይዛል::
  - የቅጥር መጠይቅ፣
  - ለክፍት የስራ ቦታው የወጣው ማስታወቂያ፣
  - የቅጥራ ቃለ ጉባኤ፣
  - የትምህርት ደረጃ ማስረጃና የስራ ልምድ፣ የምስክር ወረቀት፣
  - የተቀጣሪው የጤንነት ማረጋገጫ፣
  - የተቀጣሪው የሙከራ ጊዜ ቅጥር ደብዳቤ፣
  - የስራ ዝርዝር ተግባራት፣
  - ተቀጣሪው በሙከራ ጊዜ ያገኘው የስራ አፈጻጸም ውጤት፣
  - የተቀጣሪው የህይወት ታሪክ ቅፅና የቅጥር ማመልከቻ፣
  - የተቀጣሪው ሶስት ተመሳሳይ ጉርድ ፎቶግራፎች፣

የሰው ሀይል ቅጥር እና ምልመላ

ECCSA

- ለተወሰነ ሥራ/ጊዜ የሚደረግ የስራ ውል
- ለተወሰነ ጊዜ ወይመ ሥራ የሚደረግ የስራ ውል በሚከተሉት ምክንያቶች ይሆናል
  - ሰራተኛው የተረቀጠረበት ስራ በተወሰነ ጊዜ የሚያልቅ ሲሆን፣
  - በፈቃድ፣ በህመም ወይም በሌላ ማንኛውም ምክንያት ለጊዜው ከስራ የተለየን ሰራተኛ ለመተካት፣
  - ስራ መብዛት በሚኖርበት ጊዜ ስራን ለማቃለል፣
  - አልፎ አልፎ የሚሰሩ ማለትም ስራው gሚ ሆኖ እየተgረጠ ስራው በሚኖርበት ግዜ ብቻ ስራ ለመስራት፣
  - አንዳንድ ጊዜ የሚሰራ ስራ ማለትም gሚ ስራ ያልሆነ በሚያስፈልግበት ጊዜ ብቻ የሚሰራ ስራ ለመስራት፣
  - ላልተወሰነ ጊዜ የስራ ውል በተደረገበት የስራ መደብ ላይ ሰራተኛ በድንገት ለዘለቄታው በመለየቱ ለግዜው ስራ ለማሰራት፣

የሰው ሀይል ቅጥር እና ምልመላ

ECCSA

- ለተወሰነ ሰራ/ጊዜ የተቀጠረ ሰራተኛን ስለሚሰናበትበት ሁኔታ
  - የውል ማለቂያ ግዜ ከመድረሱ ቢያንስ ከሰባት የስራ ቀናት በፊት ማሳወቅ
  - በቀሪው ግዜ ውስጥ ሰራተኛው ስራውን አጠናቆ ማስረከቡን በማረጋገጥ
  - ለስራ ወጪ የተደረጉ ንብረቶችና የስራ መሳሪያዎች እንዲያስረክብ በማድረግ
  - ከማናቸውም እዳ ነፃ መሆኑን በማረጋገጥ
  - ለሰራበት ጊዜ ደመወዝ እንዲከፈል አድርጎ የስራ ውል ማለቁኝ የሚገልጽ ደብዳቤ ሰጥቶ ያሰናብተዋል

የሰው ሃይል ቅጥር እና ምልመላ

ECCSA

ትውውቅ

- አዲስ ተቀጣሪ ስራ ከመጀመሩ በፊት
  - ቢሮና ለስራ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች ፣
  - ስለ ድርጅቱ አላማና ተግባራት ፣
  - ስለ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ፣
  - እንዲሁም ከሚመደቡበት የስራ ክፍል ሰራተኞች ከሚሰራው ስራ እና ሌሎች ከተቀጠረበት ስራ ጋር የሚገኙ ጉዳዮችን በተመለከተ በቅርብ ሀላፊው አማካኝነት ገለጻና ትውውቅ ይደረግለታል::

የመፈጸም አቅም (Performance Management)

ECCSA

- የመፈጸም አቅም ማለት ሰራተኞች ከላይ የተቀመጠው የሚሻሻል የመፈጸም አቅም እንዲያዳብሩ የሚደረግበት ሂደት ነዉ
- የመፈጸም አቅም ለማጎልበት የምንከተለው ሂደት
- የመፈጸም አቅም እቅድ
  - የስራ ዝርዝር
  - የረጅም እና አጭር ጊዜ እቅድ
  - ቁልፍ ግቦች
  - ግቦቹ እንዴት እንደሚለኩ
  - ግብረመልስ መሰብሰብ
  - ማጽደቅ
- የስራ ምዘና

- የሥራ አፈጻጸም ምዘና ሠራተኛው ያለውን የአዕምሮና የአካል ችሎታዎቹን በመጠቀም ከድርጅታችን እቅድ አኳያ በተወሰነ የሥልጣን ኃላፊነት ክልል ውስጥ የተሰጠውን ተግባራት ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ማከናወኑን ለማወቅ በተወሰነ ወቅት የሚደረግ ሥርዓት ያለውና ከአድልዎ ነፃ የሆነ ግምገማ ነው።

የመፈጸም አቅም (Performance Management)

ECCSA

- የሥራ አፈጻጸም ምዘና አላማዎች፤
  - የሥራ ውጤትን መሠረት በማድረግ ጠንካራና ውጤታማ ሠራተኞችን ለይቶ ለማወቅ እና ለማበረታታት፣
  - በእያንዳንዱ የሥራ ዘርፎች ድክመት የሚታይባቸውን ሠራተኞች ለይቶ በማወቅ ጉድለታቸውን እንዲያርሙ ተገቢውን ስልጠና እና ድጋፍ ለመስጠት እንዲሁም የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ፣
  - ሠራተኛው የራሱን የሥራ እንቅስቃሴ ከሌሎች የሥራ ባልደረቦቹ ጋር በማነፃፀር ራሱን ለማሻሻል እንዲችል ለማበረታታት፣
  - የድርጅቱን የሥልጠና ፍላጉት መጠንና ዓይነት በመረዳት የሥልጠና እቅድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ለማድረግ፣
  - በሠራተኛ ምልመላ፣ ምደባ፣ እድገትና ዝውውር ሥርዓት ላይ ሊደረጉ የሚገባቸውን ማሻሻያዎች ለመጠቆም እንዲያስችል፣

    ሠራተኛው በያዘዉ የሥራ መደብ ላይ ከፍተኛ ውጤት በማስገኘቱ ለሚቀጥለው የሥራ መደብ ብቁ ሆኖ በዕድገት ተወዳድሮ እንዲመደብ አንዱ መመዘኛ መስፈርት በመሆኑ፣

የመፈጸም አቅም(Performance Management)

ECCSA

- የሥራ አፈጻጸም ምዘና አሞላል፣
- የሥራ አፈጻጸም ምዘና ሪፖርት የሚሞላው ኃላፊ፣
  - የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ቅፅን ዓላማ እና የአሞላል ሥርዓት በትክክል በመረዳት በጥንቃቄ እና በሃቀኝነት የመሙላት፣
  - የሥራ አፈጻጸም ምዘና ሪፖርት ከተሞላ በኋላ ሠራተኛው ስለምዘናው ያለውን አስተያየት በጽሁፍ እንዲያሰፍርና እንዲፈርም የማድረግ ኃላፊነት አለበት፣
  - ሠራተኛው የሥራ አፈፃፀም ቅፅ አሞላል ላይ ቅሬታ ካለው ቅሬታውን ለሚመለከተዉ ሀላፊ በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል። ቅሬታውም የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጠዋል።ሠራተኛው በሥራ አፈፃፀም ምዘና ላይ ያቀረበው ቅሬታ ትክክለኛ ሆኖ ከተገኘ እንዲስተካከል ይደረጋል።
  - የሠራተኛው የምዘና አማካይ ውጤት እየታየ ዓመታዊ የደመወዝ ጭማሪ እንዲያገኝ ሌሎች መስፈርቶች(የስራ ልምድና ተገቢዉ ለመደቡ የተጠየቀ የትምህርት ዝግጅት) መሟላታቸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በደረጃ ዕድገት እንዲወዳደር ይደረጋል።

የመፈጸም አቅም (Performance Management)

ECCSA

- የሥራ አፈጻጸም ምዘና አሞላል፣
- የሥራ አፈጻጸም ምዘና ሪፖርት የሚሞላው ኃላፊ፣
  - የሠራተኛውን የሥራ ውጤት በአንዳንድ አጋጣሚዎችና ግላዊ ግንኙነቶች ሳይመራ በተጨበጭ የድርጅቱን ዕቅድ ከመተግበር አንፃር ለመመዘን፣
  - ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በየጊዜው በማስታወሻ መዝግቦ በመያዝ፣
  - በሥራ ሂደት በችሎታ ማነስም ሆነ በሌላ ምክንያት የሚያሳያቸውን ደካማ ጎን እንዲያሻሽል በወቅቱ ተገቢ ምክር በመስጠትና በማስታወሻ በመያዝ፣
  - ደካማ ጎኖችን እንዲያሻሽል የተሰጠውን ምክር ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ያሳየውን ለውጥ በማጤን፣
  - ሠራተኛው በሥራ መደቡ ከተሰጡት ተግባራት በተጨማሪ ለድርጅቱ አጠቃላይ እድገትና ጤናማ አካሄድ ያለውን እና የሚያደርገውን አስተዋጽኦ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣

የመፈጸም አቅም (Performance Management)

ECCSA

- የመፈጸም አቅም ስልጠና”
  - ስልጠና
  - ምክክር
  - ስብሰባዎች
- የመፈጸም አቅም ትግበራ”
  - ማበረታቻ
  - ለቀጣይ እቅድ መዘጋጀት

ደሞዝ እና ጥቅማጥቅም(Remuneration)

ECCSA

- ደሞዝና ጥቅማ ጥቅም ማለት፣ ሰራተኞች ለድርጅታችን ላበረከቱት አስተዋ ጽኦ የሚከፈላቸው ክፍያ ነው
- ደሞዝ
  - በየወሩ የሚከፈል
  - ጡረታ የሚቆረጥበት
  - ግብር የሚከፈልበት
- ጥቅማጥቅም
  - የጡረታ
  - የዉሎ አበል
  - የቤት
  - የትራንስፖርት
  - የህክምና

ደሞዝ እና ጥቅማጥቅም(Remuneration)

ECCSA

- ማበረታቻ
  - ከመፈጸም አቅም ጋር የተያያ መሆኑ
  - አላማዉም የመፈጸም አቅም ቀጣይ እንዲሆን ለማድረግ ነዉ

- ደሞዝ እና ጥቅማጥቅም በሚዘጋጅበት ወቅት
  - ዉስጣዊ ፍትሀዊነት
  - ዉጫዊ እኩልነት

የንግድ ዕድገት አቅጣጫን ለማስተካከል ጠቃሚ ምክሮች

ECCSA

- ግልጽ በሆነ የእድገት ዓላማዎች ይጀምሩ
- የእርስዎን ሃሳቦች እቅዶች እና ሂደቶች ይመዝግቡ
- ንግድዎን ከመጀመሪያው ጀምሮ መደበኛ ያድርጉት
- የእውቀት ክፍተቶችን ለመዝጋት በባለሙያዎች ይጠቀሙ
- ንግዱን ሙያዊ ያድርጉት
- የተተኪ እቅድ ይኑርዎት
- በተቻለ መጠን አውታረ መረብዎን ያጠናክሩ
- ንግዱ እያደገ ሲሄድ በአግባቡ ለመያዝ አሰልጣኝ እና አማካሪ ይፈልጉ
- ፈጠራን ለንግድዎ ዋና እሴት አድርገው ይቀበሉ
- ንግድዎን በዘላቂነት ያካሂዱ

ማጠቃለያ

ECCSA

- ይሄ ስልጠና ድርጅትን ዉጤታማ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ዋና ዋና ነጥቦች የተካተቱበት በመሆኑ ተበዳሪዎች ብድር ከማግኘታቸዉ በፊት ስልጠናዉን መዉሰድ ይኖርባቸዋል።

- ስልጠናዉም ተበዳሪዎች ዉጤታማ ሆነዉ ብድራቸዉን በተገቢዉ ሁኔታ መክፈል እንዲችሉ ያግዛቸዋል።